
# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-10/2017 የነበረው
# የአየር ሁኔታ ግምገማ

በኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ የቆየ ሲሆን፤ ወቅታዊውን ዝናብ በመደበኛ ሁኔታ የሚያገኙት የደቡብ፣ የደቡብ ምሥራቅ፣ የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች በመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናት ዝናቡ በቦታና በመጠን ረገድ  የቀጠለ ቢሆንም፤ በመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ግን ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ቀስ ቀስ በመዳከማቸው በዚህ ወቅት ዝናብ በሚጠበቅባቸው በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመጠንንም ሆነ በስርጭት ቀንሶ ተስተውሏል፡፡  በመሆኑም አብዛኛዎቹ አካባቢዎች በደረቅና ቀዝቃዛ የአየር ተፅዕኖ ስር ነበሩ፡፡ ከዚህም ሌላ በመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናት ለዝናብ መፈጠር መንስኤ የሆኑት የአየር ሁኔታ ገጽታዎች አንጻራዊ በሆነ መልኩ በመጠናከራቸው ምክንያት የደመናው ሽፋን ወደ መካከለኛውና ሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ ሥፍራዎች በመስፋፋት በጥቂት ቦታዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንዲጥል አስተዋፅዖ አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ የተመዘገበ ሲሆን፤ በጥቂት ቦታዎች ላይም ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል። ለመጥቀስም ያህል በምዕራብ አባያ 106.0፣ በሞያሌ 69.7፣ በቦሬ 39.4፣ በአዴት 43.2፣ በአቦቦ 39.5፣ በሀገረማርያም 63.6፣ እና በዶሎመና 47.3 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ እምብዛም ያልተጠናከረ ቢሆንም፤ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በአንዳነድ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ከነዚህም መካከል ለመጥቀስ ያህል በወገል ጤና 2.9፣ በደብረ ብርሃን 1.4፣ በመሀል ሜዳ 2.2፣ በሀረማያ 4.0፣ በቡኢ 3.0፣ በአምባ ማርያም 3.8  በሾላ ገበያ 4.5 እና በእነዋሪ 5.0 በዲግሪ ሴልሽየስ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከ5-109 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ምስራቅ ትግራይ፤ ከአማራ አገዋዊ፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ከኦሮሚያ፤ምዕራብና ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ጅማ፣ ጥቂት የአርሲና የባሌ እንዲሁም የቦረና ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል-ጉሙዝ የመተከል ምስራቃዊው ክፍል፤ ከጋምቤላ ዞን 1ና 2፤ አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ በሶማሌ ክልል የሚገኙት የደገሀቡር፣ የዋርዴር፣ የቆራሄ፣ አፍዴር፣ የጎዴ እና የሊበን ዞኖች ከ2-8 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ እና ፀሐያማ ሆነው ቆይተዋል (ካርታ 1 እና 2)።

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር ምስራቅ ትግራይ፤ ከአማራ አገዋዊ፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፤ ከኦሮሚያ ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ጅማ፣ የአርሲና የባሌ እንዲሁም የቦረና ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል-ጉሙዝ የመተከል ምስራቃዊው ክፍል፤ ጋምቤላ፤ አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤እንዲሁም በሶማሌ ክልል የሚገኙት የደገሀቡር፣ አፍዴር፣ የጎዴና የሊበን ዞኖች መደበኛ እና ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት አብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ እና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ ተስተውሎባቸዋል( ካርታ 3)።


ካርታ1 ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ2   እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2017 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




**ካርታ3   እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር**



# <u>እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1- 10/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ</u>

በኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ተስተውሏል። ይህም በመሆኑ በዚህ ጊዜ የሰብል ስብሰባቸውን በሚያካሄዱ በአንዳንድ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች የነበረው ደረቅ የአየር ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር፡፡ በሌላ በኩል በምዕራብ የነበረው እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታ እንደነበረው እሙን ቢሆንም፤ ለሰብል ሰብሰባ እና ድህረ ሰብል ሰብሰባ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረዉ። በሌላ በኩል በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው በመሆኑ የተገኘዉ እርጥበት ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ዘግይተው ለተዘሩ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት እንዲሁም በቆላማው አካባቢ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋጽዕ እንደነበረው ይታመናል።


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2017 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1- 10/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

እ.ኤ.አ 1-10 ኖቬምበር 2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ እርጥበት በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ ተፋሰሶች ላይ የነበራቸው ሲሆን፣ የተቀሩት የአገሪቱ ተፋሰሶች ደረቃማ ሁኔታ ተስተዉሎባቸዋል$ ይህንን ተከትሎ በጥቂት የአባይ ደቡባዊ ጫፍ፣ የታችኛው ኦሞጊቤ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ስምጥሸለቆ እንዲሁም የገናሌዳዋ ምዕራባዊው አጋማሽ ተፋሰሶች ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል$ በተጨማሪም የገናሌዳዋ የምስራቃዊው አጋማሽ፣ ጥቂት የመካከለኛው ስምጥሸለቆ፣ በጥቂት የመካከለኛው አባይ፣ የላይኛው ባሮአኮቦ፣ የመካከለኛው ኦሞጊቤና የአባይ የመካከለኛውና ደቡባዊው ክፍል ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት ነበራቸው$ የተቀሩት የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተስተውሏል$

ካርታ 5.　　እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1- 10/2017 በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



# <u>እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11-20/2017 የሚኖረው</u>

# <u>*የአየር ሁኔታ አዝማሚያ*</u>

በመደበኛ ሁኔታ በኖቨምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝን ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሰሜን፣ የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የመካከለኛው እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ይዘወተራል፡፡ በተጨማሪም የደቡብ ምዕራብ እና የደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ሊጠናከር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት <u>ከኦሮሚያ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ጥቂት የባሌና የአርሲ እንዲሁም የጉጂ እና የቦረና ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የደቡብ ኦሞ እና የሰገን ሕዝቦች፤ እንዲሁም በሶማሌ ክልል የሚገኙት የደገሀቡር፣ የፊቅ፣ የዋርዴር፣ የቆራሂ፣ አፍዴር፣ የጎዴ እና የሊበን ዞኖች በተለያዩ ሥፍራዎቻቸው ላይ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፤ አልፎ አልፎም በጥቂት ኪስ ቦታዎቻቸው ላይ ከመደበኛው በላይ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ፡፡</u>

# <u>እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 11-20/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ</u>

በኖቨምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን በትንበያው ተገልጿል፡፡ ይህም ሁኔታ የመኸር ሰብሎችን ለመሰብሰብ አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ አጋጣሚውን በመጠቀም አርሶ አደሩ የደረሱ ሰብሎችን በቶሎ መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ በሌላ በኩል የሰሜንና ሰሜን ምስራቅ፣ የምሥራቅ፣ የመካከለኛው እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሚጠበቀው የሌሊቱና

የማለዳው ቅዝቃዜ ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም በደቡብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚኖረው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ በሰብል ስብሰባና ድህረ ስብሰባ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ በደቡብ የተለያዩ ሥፍራዎች ላይ በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ እርጥበት ስርጭት ሊኖረው እንደሚችል ይገመታል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚገኘዉ እርጥበት ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት እና ጥምር ግብርና ለሚያካሂዱ የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲሁም ዘግይተው ለተዘሩ ሰብሎችና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ቋሚ ተክሎች የሚያስፈልጋቸውን የእርጥበት አቅርቦት በመጠኑም ቢሆን የተሻለ ሁኔታን የሚፈጥር ሲሆን፣ ይህም የእርጥበት ሁኔታው ወደ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሚያደርገው መስፋፋት በአርብቶ አደርና በከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል የውሃ እጥረት የሚታይባቸው አካባቢዎች የሚገኘውን የእርጥበት ብክነት ለመቀነስ የሚረዱ ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ ይመከራል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11-20/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ውስጥ በደቡብና በደቡብ ምዕራብ አጋማሽ ከሚገኙት ተፋሰሶች በስተቀር በተቀሩት በአባዛኛዎቹ ዋና ዋና ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሃያማና ነፋሻማ ሁኔታ አመዝኖ እንደሚቀጥል ትንበያው ይጠቁማል$ በዚህ መሰረት ምስራቃዊ አጋማሽ የባሮአኮቦ እና የመካከለኛው ኦሞጊቤ አዋሳኝ ተፋሰሶች፣ የታችኛው ስምጥሸለቆ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ዋቢሸበሌ፣ ኦጋዴን፣ አብዛኛው ገናሌዳዋና ጥቂት የላይኛው ዋቢሸበሌ ተዋሳኝ ከፍተኛ ቦታዎች የሚገኙ ተፋሰሶች በአመዛኙ ከመደበኛው ጋር ተቀራረበ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፣ አልፎ አልፎ በጥቂት ኪስ ተፋሰሶች ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል$ በእነዚህ ተፋሰሶች ላይ የሚገኘው ዝናብ የውሃ እጥረትን ለመቋቋም ዘለቄታ እንዲኖረው በተለያየ መንገድ የዝናብ ውሃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም የውሃን ግብዓት ማሻሻል አስፈላጊ ነው$ በተቀሩት በአብዛኛው የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሁኔታ ቀጣይነት ያለው በመሆኑ ውሃን ለብክነት ከሚያጋልጡ ነገሮች መጠበቅ አስፈላጊ ነው$